ስሐ፡ገብቶ፡የሚዶኙም፡አሉ፡
የቀደመውን፡ኃጢአታቸውን፡
ጠልተው፡የረከሰች፡የዝሙ
ታቸውን፡ልብስ፡የተዉ፡አሉ፤
ያዕ፡፭፡፲፱፡፳፡ራእ፡፫፡፬፤
፷ መድኃኒታችን፡እግዚአብሔ
ርም፡ያለ፡ኃጢአት፡ይጠብቃ
ችሁ፡ዘንድ፡ንጹሐን፡ሁናችሁ
ም፡በጌትነቱ፡ፊት፡በደስታ፡ያ
ቆማችሁ፡ዘንድ፡ይቻለዋል፤፩
ተሰ፭፡፳፫፡ፊል፡፩፡፲፤
፷፩ በጌታችን፡በመድኃኒታችን፡በ
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሥልጣን፡
ለርሱ፡ምስጋና፡ይሁን፤
ጌትነትም፡ኃይልና፡ሥልጣን
ም። ዓለም፡ከተፈጠረ፡ጀምሮ፡
ዛሬም፡ዘወትርም፡እስከ፡አሚ
መጣው፡ሁሉ፤ አሜን፤
የያዕቆብ፡ወንድም፡የይሁዳ፡
መልክት፡ተፈጸመ፤ሮሜ
፲፯፡፳፯፡፩፡ጢሞ፡፩፡፲፯፤ ፤
ለእግዚአብሔር፡ምስጋና፡ይ
ግባው፤ ፤ ፤ ፤ ፤

ራእዩ፡ለዮሐንስ።
የመጸናኛቱ፡የቍስጥንጥንያ፡
ኤጲስ፡ቆጶስ፡ዮሐንስ፡አፈወርቅ
ተስደ፡የነበረ፡ጊዜ፡ያገኘው።

ምዕራፍ፡፩።

የቍስጥንጥንያ፣ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዮሐንስ፡
አፈ፡ወርቅ፣ ፍጥሞ፡በምትባለው፡ደሴ
ት፡ተሰዶ፡ሳለ፤ዮሐንስ፡ወንጌላዊ፡ያየው፡የ
የራዕይ፡መጽሐፍ፡አግኝቶ፡እንደ፡ጻፈው፤ራ
እዩም፡የተገለጸለት፡እሑድ፡ቀን፡እንደ፡ሆነ—
፩ ዮሐንስ፡ወንጌላዊ፡ያየው፡ራ
እይ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡እንዲ፡
አየው፡መጠን፡ፈጥኖ፡ይሆን፡ዘ
ንድ፡ያለውን፡ከዚያም፡በኋላ
የሚመጣውን፡ለባሮቹ፡ይገ
ልጥላቸው፡ዘንድ፡እግዚአብ
ሔር፡የገለጠለት፡ቃል፤ ፲፱፡ምዕ፳
፪ ፳፪፡፯፡፯፤ በመልአኩ፡እጁ፡ወደ
ባርያው፡ወደ፡ዮሐንስ፡የላከው
ስለ፡እግዚአብሔር፡ቃልና፡ስለ
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፣ምስክር፡ግ
የው፡ሁሉ፡ለይ፡ምስክር፡የሆ
ነ፡ቍ፱፡ምዕ፡፯፡፱፤
፫ የሚያነበው፡የትንቢቱንም
ቃል፡የሚሰማ፡በውስጡ፡የቱ
ጻፈውንም፡የሚጠብቅ፡የተ
መሰገነ፡ነው፡ዘመኑ፡ቀርቧ፡ነ
ውና፤ምዕ፳፪፡፯፡ምዕ፳፪፡፲፤
፬ ከዮሐንስ፡በእስያ፡ላሉ፡ለሰባቱ
አብያተ፡ክርስቲያናት፡ተጻፈ
ቀድሞ፡ከነበረው፡አሁንም